እኔም ታዝቤሃለሁ

በየድረ ገጹ የሚወጡ ጽሁፎችን በተቻለኝ ብከታተልም ጽፌ ግን አላውቅም። የሀገራችንን የፖለቲካ ሁኔታም በተቻለኝ አቅም እከታተላለሁ። ሰሞኑን ደግሞ የግንቦት 7፡ ኦነግና ኦብነግን የጋራ ግንኙነት አስመልክቶ ያለውን ውዝግብና የሚሰጡ አስተያየቶች እከታተላለሁ። ለመጻፍ ግን ያነሳሳኝ በዚህ ሁለት ቀን ያነበብኩት «ዛቻና ስድብ ፤ የኢሕአፓ ፖለቲካ» በሚል ርዕስ የተጻፈውና ኢትዮሚዲያ ደረ-ገጽ ላይ የወጣው የአቶ በቀለ ንጋቱ ጽሁፍ ነው።

ሰሞኑን ዶር ጌታቸው በጋሻው በአወጡት ጽሁፍና ከዚያም በፊት በቨርጂኒያ የግንቦት 7ና የኦነግ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ያደረጉትን ንግግር ስብሰባው ላይ በመገኘት ተከታትያለሁ። በአለፈው ዕሁድም በCurrent Affairs መወያያ ፓልቶክ ቀርበው የሰጡትን ቃለ ምልልስ አድምጫለሁ። የቨርጂንያውን ስብሰባና ዶር ጌታቸው ባለፈው ሰሞን ያቀረቡትን ጽሁፍና በራስ አሉላ አባ ነጋ የፓልቶክ ክፍል ቀርበው የሰጡትን ውይይት አስመልክቶ በተለያየ ጊዜ የተጻፉ ጽሁፎች አንብቤሃለሁ። ዶር ጌታቸው በተለይ የኦነግንና የኦብነግን የመገንጠል ጥያቄ የመደገፍ አዝማሚያ ቢያሳዝነኝም ለሚሰጥባቸው ተገቢ ትችት መልስ መስጠት ሲገባቸው አቅጣጫውን ለማሳት የሚደረገው አካሄድ ስላሳዘነኝ ነው የጻፍኩት።

በመጀመሪያ ዶር ጌታቸው በስልክ ቴክስት ከተደረገላቸው የማን ስልክ እንደሆነ ባያውቁት እንኳ ስልክ ቁጥሩ አብሮ እንደሚደርሳቸው እርግጠኛ በመሆኔ የማን ስልክ መሆኑን ማረጋገጥ ቀላል ነው። ደረሰኝ ያሉት የዛቻ የስልክ መልዕክትም እውነት ከሆነ እራሳቸው መጻፍና ማሳወቅ ምን አቃታቸው? ለምን ለሌላ ሰው ልከው ወይም አሳውቀው እንዲጻፍላቸው ፈለጉ? የሚለው ጉዳይ በጭንቅላቴ ሲብላላ ያገኘሁት መልስ ዶር ጌታቸው እየቀረበባቸው ባለው ትችት መውጫ ቀዳዳ ሲያጡ አቅጣጫ ለማሳት ያደረጉት መሰለኝና ነው የጻፍኩት። ዶር ጌታቸው ብልጥ ሆንኩ ሲሉ ከሳቸው የባሰ ቆቅ እንዳለ ቢረዱ ጥሩ ይመስለኛል። ስለ ኦነግ በቅኝ ከያዘችን ኢትዮጵያ መላቀቅ ነው ትግላችን ሲጠየቁ፤ ኢሕአፓ ሰደበኝ እያሉ አጀንዳውን ወደ ሌላ ለመውሰድ ከመጣር ከገቡበት ማጥ ወይ መውጣት አለያም አግባብ የሆነ መልስ መስጠት ነው አስፈላጊው። መልሱም ካለቀቦት ዝም ብሎ መቀመጥ። ስለ ሀገር አንድነትና ስለ ኢትዮጵያ የሚጽፈው ዜጋ ልጻፍ ካለ አያልቅበትም። ስለ መከፋፈልና ግንጠላ ግን መጻፉም ያስቸግራልና ከአፈርኩ አይመልሰኝ ጉዞዎን ትተው ልቦና ቢገዙ ጥሩ ይመስለኛል። የኦነግና የግንቦት 7ን ግንኙነት እንዴት ያዩታል? ተብሎ ሲጠየቁ፤ ኢሕአፓ አስቸገረኝ ማለቱን ይተዉና የተጠየቁትን ቢመልሱ ጥሩ ነው። ሌላው መረዳት ያለብዎት ባንጽፍም፡ ባንናገርም  የሀገራችን ጉዳይ የሚያሳስበንና የምንከታተል በርካታዎች እንዳለን ሊገነዘቡ ይገባዎታል። ብዙ ብጽፍ ደስ ባለኝ ግና ለዛሬ በዚሁ ላብቃ።

ኢትዮጵያችንን ሁላችንም እንጠብቃት።

አመሰግናለሁ።

ጣይቱ።